ውርስ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሕገመንግስቱ እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 10 መሠረት የተሰጠው ስልጣን በአዋጁ በዝርዝር በተመለከቱት እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበትን የመጨረሻ ውሳኔ ማረም ነው፡፡ ይህን ስልጣኑን መሠረት በማድረግ ሰበር ሰሚ ችሎቱ በበርካታ ጉዳዮች ላይ የሕግ ትርጉም ሲሰጥ ቆይቷል፡፡ በዚህም በአገሪቱ ውስጥ ወጥ የሆነ የሕግ አረዳደር እና አተርጓጎም እንዲኖር በማድረግ ሕገመንግስታዊ ግድታውን ሲወጣ ቆይቷል፡ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ከአምስት ባላነሱ ዳኞች የተሰጠ የሕግ ትርጉም ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በየትኛውም ደረጃ በሚገኝ የፌዴራልም ሆነ የክልል ፍርድ ቤት አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 26(1)እና(4) ላይ እንደተገለጸው አምስት ዳኞች የተሰየሙት የሰበር ሰሚ ችሎት በባለጉዳዮቹ አመልካችነት ወይም በችሎቱ በራሱ አነሳሽነት ቀድሞ የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም በተለያዩ ምክንያቶች ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ከሰባት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታይ በቂ እና አሳማኝ ምክንያቶችን ተንትኖ በመግለጽ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡ በዚህ አግባብ በሰባት ዳኞች የተሰጠው ውሳኔም ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ አስገዳጅ ነው፤ በዚህ አግባብ መሠረት ከሰባት ያላነሱ ዳኞች የተሰየሙበት የሰበር ችሎት ቀድሞ የሰጠውን የሕግ ትርጉም ከሰባት ባላነሱ ዳኞች በተመሳሳይ ጭብጥ በሌላ ጊዜ ሊሻሻል ይችላል በማለት የደነግጋል፡፡ (አስቀድሞ የተሰጠው ውሳኔ በሰባት ዳኛ ሊለወጥ ይገባል ወይስ አይገባል ለማለት የሚያስችሉ ምክንያቶች የትኞቹ ናቸው የሚለው በአዋጁ ላይ አመላካች ነገር እንዳልተቀመጠ ልብ ይሏል)

ሰበር ሰሚ ችሎቱ በተለያዩ ጊዜ የውርስ ይርጋን አስመለክቶ የሰጣቸው ውሳኔዎች እርስ በእርስ ያላቸው መስተጋብር ምንድነው የሚለውን ለመለየት ውሳኔዎቹን በአግባቡ ማየት ይጠይቃል፡፡ በዚህ ዓመት በሰባት ዳኞች በሰ.መ.ቁ 243973 ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔም በአግባቡ ሊታይ የሚገባው ሌላው ውሳኔ ነው፡፡ በሰባት ዳኞች ታይቶ የውርስ ንብረት ከፍፍልን አስመልክቶ ቀደም ሲል ተይዞ የነበረውን አቋም በመቀየር ውሳኔ ሲሰጥ ከውሳኔው ሰጪ ዳኞች አንዷ ነበርኩ፡፡ ይህ ውሳኔ በሌላ ሰባት ዳኞች ታይቶ ሊለወጥ ይገባል ወይስ አይገባም ለማለት በተጨባጭ በማሕበረሰቡ ዘንድ ያለውን የኑሮ መስተጋብር እና እየመጣ ያለውን ውጤት በአግባቡ ማጤን ይፈልጋል፡፡ ቀደም ሲል ሰበር ሰሚ ችሎቱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1000 መሠረት በተለያዩ መዛግብት ላይ የሰጣቸውን ውሳኔዎች እና በሰባት ዳኞች ታይቶ የተሰጠው ውሳኔ አጭር ማጠቃለያ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- *በመሠረቱ ይርጋ መብቱ ወይም ጥቅሙ የተነካበት ሰው በሌላ ሰው ላይ የሚያቀርበውን ክስ፤ አቤቱታ ወይም የይገባኛል ጥያቄ አስመልክቶ በሕግ ተለይቶ የተቀመጠ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ ነው፡፡ የይርጋ ጽንሰ ሐሳብ ሶስት መሠረታዊ ምክንያቶችን የያዘ ነው፡፡ እነኚህም፦*
    1. *ክሳሽ በተገቢው ትጋት እና በቂ ምክንያት መብቱን እንዲጠይቅ ማስቻል እና ዳተኛ የሆነ ተከራካሪ ወገን እንዳይኖር ማድረግ፤*
    2. *ተከሳሽ በጣም ዘግይተው የሚመጡ ክሶችን ለመከላከል የሚያስችሉትን ማስረጃዎች እንዳያጣ ማድረግ፤*
    3. *ዘግይው የሚቀርቡ ክሶች ዓላማቸው ፍትሕ ከማስገኘት ይልቅ ለበቀል እና ለማጥቂያ እንዳይውሉ ማድረግ ናቸው*

የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1000(1) ድንጋጌ ከሳሹ መብቱን እና የውርስ ንብረቶች በተከሳሹ መያዛቸውን ካወቀ ሶስት ዓመት ካለፈ በኋላ ስለ ወራሽነት ጥያቄ የሚቀርበው ክስ ተቀባይነት ለማግኘት አይችልም በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ ሕግ ንዑስ (2) ድንጋጌ ደግሞ እንደዚሁም ሟቹ ከሞተበት ወይም በመብቱ ለመሥራት ከቻለበት ቀን አንስቶ አስራ አምስት ዓመት ካለፈ በኋላ ከዘር የወረደ ርስት ካልሆነ በቀር የተባለው የውርስ ጥያቄ ክስ በማናቸውም አስተያየት ቢሆን ተቀባይነት ማግኘት አይችልም በማለት ይደነግጋል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ በፊቱ በቀረቡ በርካታ ጉዳዮች ላይ በውርስ ይርጋ ላይ በርካታ የሕግ ትርጉም ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

- *በሰ.መ.ቁ 25664 በሰጠው ውሳኔ ወራሽ የሆነ ሰው የውርስ ንብረቱን ለማስመለስ ወራሽ ባልሆነ ሰው ላይ የሚያቀርበው ክስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1677 እና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 1845 መሠረት በ10 ዓመት ይርጋ የሚታገድ ነው በሚል ወስኗል፡፡*
- *በሰ.መ.ቁ 44025 በሰጠው ውሳኔ ወራሾች በጋራ ይዘው ሲያስተዳድሩት ወይም ሲጠቀሙበት የነበረ የውርስ ንብረት ለመጠየቅ የቀረበ ክስ ላይ የቀረበ የይርጋ መቃወሚያ ተቀባይነት የሌለው ነው በሚል ወስኗል፡፡*
- *በሰ.መ.ቁ 120841 በሰጠው ውሳኔ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ወራሽነት መብቱን ለአካለ መጠን ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 15 ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ የውርሱን ንብረት ለመጠየቅ በይርጋ ሊይታገድም በሚል ወስኗል፡፡ ይህ ውሳኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁ 198 እና 100(2) ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ የተሰጠ ውሳኔ ነው፡፡*
- *በሰ.መ.ቁ 224271 ጥቅምት 02 ቀን 2015 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ፦ በሰ.መ.ቁ 171038 ወራሽ በሆነ እና ወራሽ ባልሆነ ሰው መካከል ላለ የውርስ ንብረት ክርክር ተፈጻሚነት ያለው የ10 አመት ይርጋ እንደሆነ ይህ የአስር አመቱ የይርጋ ግዜ መቆጠር ያለበት አካለመጠን ያላደረሰ ሰው አካለመጠን ካደረሰበት ግዜ አንስቶ መሆኑን፤ የመዝገቡ ተጠሪ አካለመጠን ካደረሰችበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስካቀረበችበት ቀን ድረስ ያለው ጊዜ ሲታሰብ 10(አስር) አመት ያለፈው መሆኑን፤ ምንም እንኳ የወረዳው ፍርድ ቤት የተጠሪን ክስ በይርጋ ቀሪ ሲያደርግ የ15 አመት ይርጋን መሰረት ማድረጉ አግባብ ባይሆንም ክሱ በይርጋ ቀሪ መደረጉ ተገቢ ነው ሲል ወስኗል፡፡*
- *በሰ.መ.ቁ 44612 በሰጠው ውሳኔ የወራሽነት መብትን በሕግ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ያረጋገጡ ወራሾች የውርስ ንብረት ክፍፍልን ማቅረብ ጥያቄ በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ ይችላሉ በሚል ወስኗል*
- *በሰ.መ.ቁ 243973 ጥቅምት 06 ቀን 2017 ዓ.ም በ7 ዳኞች የተሰጠ ውሳኔ፦ በፍ/ሕ/ቁ. 1000 የተመለከተውን የይርጋ ጊዜ ከወራሽነት የምስክር ወረቀት ጋር በማያያዝ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ መብቱን የሚያስከብር ሰው የንብረት ጥያቄ ለማቅረብ ገደብ የሌለበት ተደርጎ የተሰጡ ውሳኔዎች አሉ፡፡ ይህን አቋም ለመፈተሸና ለተያዘውም ጭብጥ ግልጽነት እንዲረዳ የወራሽነት የምስክር ወረቀትና የወራሽነት ጥያቄ ያላቸውን መስተጋብር ግልጽ ማድረግ ይገባል፡፡ ሁለቱም ሐሳቦችን የያዙት ድንጋጌዎች በሕግ መድብሉ አንድ ክፍል ውስጥ ይገኛሉ፡፡ የይርጋ ጊዜው የተነሳው ግን ከወራሽነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ ነው፡፡ በአጠቃላይ የወራሽነት የምስክር ወረቀትን በተመለከተ በተጠቀሰው በሕግ መድብሉ ክፍል የተደነገገ የይርጋ ገደብ የለም፡፡ አንቀጽ 1000 በግልጽ የሚናገረው የወራሽነት ጥያቄ ተቀባይነት የሚያገኝበትን ጊዜ ነው፡፡ ጊዜው ተፈጻሚ የሚሆንበትን ሁኔታ የበለጠ ግልጽ ለማድረግ የወራሽነት ጥያቄ ከወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጠ ከሚቀርብ ማመልከቻ ያለውን ልዩነት ማየት ተገቢ ነው፡፡ የወራሽነት የምስክር ወረቀት ስሙ እንደሚናገረው የምስክር ወረቀት ሲሆን በተግባር የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰ/መ/ቁ. 243973 ፍርድ ቤቶች አንድ ሰው ከሟች ጋር ባለው ዝምድና ወይም በኑዛዜ መነሻነት ወራሽ መሆኑን በማረጋገጥ የሚሰጡት ውሳኔ ነው፡፡ ይህ ማስረጃ የህግ ሁኔታን የሚያረጋግጥ በውጤቱም ሕጉ የሚወሰደውን ግምት የሚያረጋግጥ እንጂ በተከራካሪ ወገኖች መካከል ላለ ክርክር መፍትሔ የሚሰጥ አይደለም፡፡*

  የወራሽነት ጥያቄ (petitio hereditatis) *ጥንታዊ ጽንሰ ሐሳብ ሲሆን አንድ ሰው ከሟች ንብረት ለመውረስ የሚያቀርበው ክስ ነው፡፡ የፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 999 እንደሚያስቀምጠው ደግሞ አንድ ሰው ወራሽነቱ*

እንዲታወቅለትና የተወሰዱት የውርስ ንብረቶች እንዲመለስለት የሚያቀርበው ክስ ነው፡ ፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ክሱ ሁለት ነገሮች የሚረጋገጥበት ነው፡፡ የመጀመሪያው የህግ ሁኔታ (status) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የንብረት መብት ነው፡፡ የመጀመሪያውን ብቻውን ያየን እንደሆነ በቁጥር በፍ/ሕ/ቁ. 996 ሊስተናገድ የሚችል ሲሆን የወራሽነት ጥያቄ ግን ከዚህም የሚዘል በመሆኑ የንብረት ክርክርም በውስጡ ይይዛል፡፡ የክሱን ውጤትም ተከሳሹ በእጁ ያለውን ንብረት እንዲመልስ መደረጉ መሆኑ በፍ/ሕ/ቁ. 1001 መመልከቱ ትኩረቱ ንብረት ላይ መሆኑ ያረጋግጣል፡፡ ስለዚህ እውነተኛ ወራሽ መሆንን ለማረጋገጥና የውርስ ንብረት ለማስለቀቅ የሚቀርብ ክስ ነው፡፡ የይርጋ ጊዜው ቅድመ ሁኔታ ስናይ ይህን ልዩነት ከግምት ያስገባ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ ክሱ እንዲቀርብ የተመለከተው ጊዜ መነሻ ከሳሽ መብቱንና የውርስ ንብረቶቹ በተከሳሹ መያዛቸውን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ የክሱ ይዘት ወራሽነት እና ንብረትን የሚመለከት የመሆኑን ያህል ይርጋውም እነዚህን መብቶች ከግምት የሚያስገባ ነው፡፡ ከሳሽ ስለአንደኛው ፍሬ ነገር (ስለወራሽነት መብቱ እና ስለንብረቱ) እውቀት ኖሮት ስለሌላኛው ላያውቅ ወይንም ስለሁለቱም ላያውቅ ይችላል፡፡ ስለመብቱ አውቆ ስለንብረቱ ላያውቅ የሚችልበት አጋጣሚ አንዱ የወራሽነት ምስክር ወረቀት ይዞ ስለንብረቱ ወይም ንብረቱ በማን እጅ እንደተያዘ ላያውቅ ይችላል፤እነዚህ ፍሬ ነገሮች ለስሌት መነሻ መሆናቸው የተመለከተ ቢሆንም ሕጉ ሚች ከሞተበት ወይም ከሳሽ ስለመብቱ መሰራት ከቻለበት ቀን አንስቶ በአስራአምስት ዓመታት ውስጥ የወራሽነት ክሱን ካላቀረበ ክሱ በይርጋ እንደሚታገድ በንዑስ 2 ደንግጓል፡፡ ስለዚህ የይርጋ ድንጋጌ ይዘትም የሚያወራው ስለምስክር ወረቀቱ ሳይሆን ስለወራሽነት ጥያቄ (petitio hereditatis) ነው፡፡ ተቃራኒ ውሳኔ በተንጸባረቀባቸው ውሳኔዎች ለወራሽነት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ውጤት የተለያየ ሲሆን የዚህ ማስረጃ መኖር ወራሽ ተደርጎ ከመገመት ባለፈ የንብረት መብት የማይፈጥር በመሆኑ ሰነዱ በህጉ ከታሰበለት ዓላማ ውጭ ውጤት መስጠት አይቻልም፡፡ በሌላ በኩል የወራሽነት ጥያቄ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰ/መ/ቁ. 243973 10 በጽንሰ ሐሳብም ሆነ በውጤት የተለየ በመሆኑና በይዘቱ በተመለከተው አግባብ የሚቀርብ ጥያቄ የጊዜ ገደብ የተቀመጠለት በመሆኑ የይርጋ ጊዜው ተፈጻሚነት በወራሽነት ጥያቄ ላይ ነው፤ስለሆነም የወራሽነት ማስረጃ መያዝ አለመያዝ ልዩነት ሳይኖረው በተጠቀሰው የሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የወራሽነት ጥያቄ ካልቀረበ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ይሆናል፡፡ የወራሽነት ጥያቄ በፍ/ሕ/ቁ. 1000 በተመለከተው የጊዜ ገደብ በይርጋ ይታገዳል፡፡ የውርስ ማጣራት ተጠናቆ ንብረቱ የጋራ ባልሆነበት ሁኔታ የወራሽነት ምስክር ወረቀት በመያዝ ብቻ የፍ/ሕ/ቁ. 1062 መሰረት በማድረግ ያለጊዜ ገደብ የክፍፍል ጥያቄ ሊነሳ አይችልም የሚል ትርጉም ተሰጥቷል፡፡

በኢትዮጲያ ባለው የማሕበረሰቡ መስተጋብር ቤተሰብ እርስ በእርሱ ከፍተኛ ቁርኝነት ያለው መሆኑ፤ በውጪ ሐገር የሚኖሩ ውርሱ የሚገባቸው ሰዎች ውርሱን ለመጠየቅ በማይችሉበት ሁኔታ ላይ ሊገኙ የሚችሉበት አጋጣሚ ያለ መሆኑ፤ ከሁለት አንዱ ወላጆች ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ በተለይም ታላላቅ ወንድሞች እና እህቶች በሕይወት ያለውን አንደኛውን ወላጃቸውን ውርሱን ለመጠየቅ የሚቸገሩ መሆኑ፤ በተለይም በሕይወት ላለው ወላጅ ክብር ሲባል ውርሱን የማይጠይቁበት በርካታ አጋጣሚዎች ያሉ መሆኑን፤ ሌሎች ትንንሽ እህት እና ወንድሞቻቸውንም በውርስ ሐብቱ እንዲጠቀሙበት እና እንዲያድጉበት ሲባል የውርሱን ክፍፍል የማይጠይቁበት ሁኔታ ያለ መሆኑን፤ ይህም በማሕበረሰቡ የዳበረ ልምድ መሆኑ፤ ይህን ልምድ

ከግንዛቤ ሳያስገቡ መወሰን በተጨባጭ የውርስ ክፍፍሉን ባልጠየቁ እህት እና ወንድሞች ላይ በቀጥታ የወላጆቻቸውን ንብረት በውርስ እንዳያገኙ የማድረግ ውጤት ያለው መሆኑን የምንገነዘበው ነው።፡

ሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰ.መ.ቁ 224271 ጥቅምት 02 ቀን 2015 ዓ.ም በሰባት ዳኛ በሰጠው ውሳኔ የውርስ ማጣራት ተጠናቆ ንብረቱ የጋራ ባልሆነበት ሁኔታ የወራሽነት ምስክር ወረቀት በመያዝ ብቻ የፍ/ሕ/ቁ. 1062 መሰረት በማድረግ ያለጊዜ ገደብ የክፍፍል ጥያቄ ሊነሳ አይችልም የሚል አስቀድሞ ወራሽነታቸውን በጋራ ያረጋገጡ ሰዎች በማንኛውም ሰዓት መጠየቅ ይችላሉ ተብሎ የተሰጠውን የሕግ ትርጉም ለውጦታል።፡

ሆኖም ከላይ በዝርዝር በጠየሰኳቸው ነጥቦች ምክንያት በሰባት ዳኛ የተለወጠው የሕግ ትርጉም ጸንቶ ሊቀጥል ይገባል ወይስ በሌላ ሰባት ዳኞች ወይም በሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ኮሚቴ አቅራቢነት በፌዴሬሽን ምክር ቤት ሊለወጥ ይገባል የሚለው አሁንም አሳሳቢ ነው።፡